በቃ መ ኑ ስለት ጻል ለወነ ዬል ስብከት አምነው በክርስቶስ ደም ለሚታመኑ ብቻ በሩ ክፍት ነው። ሮሜ.1፡16፤ ፩ቆሮ1፡18-25።

አንዳንድ ሰዎችም፡ የሞቱት ጻድቃን በእንቅልፍና በእረፍት ላይ እንዳሉ ዘንግተው በምድር በቅዱስ ቃሉ ሥርዓት በሕይወት በነበሩ ጊዜ ሲሰሩት የነበረውን የተዓምራት ተግባር ከሞት በኋላም ለማከናወን የሚችሉ አስመስለው ይናገራሉ። ከሞት በኋላ ተአምራት እንዳያከናውኑ ሞት እንደከለከላቸው፣ ተኝተውም እንዳሉና የመስማትም ኃይል እንደሌላቸው ግልጽ ነው። ገነትና ሲኦል በአንድ አካባቢ በነበሩበት ጊዜ እንኳን አይችሉም፣ ነበር። መዝ (88)፡10፣ ሉቃ.16፡19-31፣ ዕብ. 7፡20፡28 የትንሣኤ በኩር ክርስቶስ ብቻ እንጂ ሌሎች ቅዱሳን በሙሉ በገነት አንቀላፍተው ነው ያሉት። አይሰሙም በትንሳኤ ቀን ብቻ ይነሳሉ፤ በቀኝም ይቆማሉ። ኃጥዓንም ከሲኦል ይወጡና ለፍርድ በግራ ይቆማሉ። በፍርድም ቀን ዋስ ጠበቃ አቅርቦ መከራከር የለም። ማቴ 25፡31-46 ክርስቶስ ሲፈርድ በአንድ ቃል ግራና ቀኝ ተለያይተው ወደየተመደበላቸው ቦታ መሄድ ብቻ ይሆናል። የገሃነም ልጆች ወደዘላለም ስቃይ፣ ጻድቃኖች ደግሞ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ። ፩ተሰ 4፡13-18፣ ፩ቆሮ 6፡2፣ ገላ 5፡16 ክርስቲያን ሆይ! የክርስቶስን ሥጋና ደም አትናቅ። ዕብ 10፡19-31።

የእግዚአብሔር ቃል፡ "የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ፣ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?" ይላልና። ለዘላለም የተገባልህን የመዳን መንገድ ጥለህ ሊሰሙ ሊያዩም ወደማይችሉ ራሳቸውንም ሊያድኑ ወደማይ



ችሉ ወደሰዎችና ወደ ሌሎችም አማልክት እንዳትዞርና እንዳይፈረድብህ ተጠንቀቅ። እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነውና ጥቅሶችን በማስተውል አንብበህ ተረዳ። ዘጸ 22፡20፣ ሮሜ 1፡20-25፣ መዝ.(146)፡3-4 ኤር. 17፡5-8፣ ራእይ 19፡9-10። 22፡8-9፣ ምሳሌ 16፡25፣ 18፡10፣ ማቴ 11፡27-30። ዮሐ 11፡25-27፣ ሐዋ.ሥራ 4፡12።

ለዘላለም በገሃነም ከመሰቃየት ለመዳን ዋስትና ያለውን አማላጅ ኢየሱስ ክርስቶስን አጥብቀህ ብትይዝ ይሻልሃል!! ነገ ሞት እንዳይቀድምህ የመዳን ቀን አሁን ነው ይላልና አሁኑኑ ከኢየሱስ ጋር ለመስማማት ፍጠን። ፪ቆሮ 6፡2፣ ሮሜ 8፡1-2 ከሞት በኋላም ንስሐ የለም። "የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፣ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም" ይላልና፤ የራስህ ጽድቅ የእውነት ጽድቅ መስሎህ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አትጣል። ሮሜ. 10፡1-3።

አይሁዶች የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ በፍርድ ላይ እንደወደቁና በዘላለም ሞት እንደተቀጡ ልትረሳው አይገባም። እንግዲህ አስብ! ከዘላለምም ሞት ለመዳን በእግዚአብሔር መንገድ ላይ ተራመድ።

## *የመዳን ቀን አሁን ነው!!*

☎ ( 6
http://www.sayadi-al-nas.com

# አማላጅ አንድ ብቻ መሆኑን አውቃችኋል?

በአዳም መተላለፍ ምክንያት የሰው ዘር በሙሉ በክርስቶስ ሥጋና ደም መስዋዕትነት ካልሆነ በቀር በሌላ መስዋእት በማይሰረይ የሞት ዕዳ ላይ ወድቋል። ሞትም በክርስቶስ በሞት ካልሆነ በቀር በሌላ አይደ መሰስም። (ሮሜ 5፡15-21፣ ዕብ 10፡1-8፣ ፩ጴጥ 1፡18-21፣ ኢሳ 25፡8)

የገሃነም እሣትን ሞት የሚያስከትል መተላለፍ በሄዋን ምክንያት ከተፈጸመ በኋላ እግዚአብሔር ከአንቺ የሚወለደው የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል ያለውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ሲል ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወለደ። ዘፍ. 3፡15፣ ገላ 4፡4።

በኢሳይያስም አፍ በቀራኒዮ ተራራ ላይ ሊያደርገው ያሰበውን ቃል ኪዳን ሲያበስር፡ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሁሉ በዚህ ተራራ ላይ ታላቅ የሰባ ግብዣ ያደርጋል። በዚህም ተራራ ላይ በወገኖች ሁሉ ላይ የተጣለውን መጋረጃ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋውን መሸፈኛ ያጠፋል። ሞትን ለዘላለም ይውጣል ጌታ እግዚአብሔርም ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፣ የሕዝቡንም ስድብ ከምድር ሁሉ ላይ ያስወግዳል እግዚአብሔር ተናግሮአልና" በማለት የገሃነም ሞትን በክርስቶስ ሞት እንደዋጠው ያረጋግጥልናል። ኢሳ 25፡6-8።

በክርስቶስ ሥጋ መቆረስና በደሙ መፍሰስ ምክንያት ስለሞት ፍርሃት በባርነት ታስረን የነበርን ሁላችን ከዲያብሎስ የማስፈራራት ቀንበር ነጻ አወጣን። ዕብ 2፡14።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር አማላጅና ተማላጅ ሊሆን እንዴት ይችላል? ይላሉ። እግዚአብሔር በልጁ ሥጋና ደም የዘላለም ሕይወት ዋስትና ቃል ኪዳን እንደገባልን ይረሳሉ። «ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፣ በመጨረሻም ቀን አስነሣዋለሁ» የሚለውን ቃልኪዳን ወደ ጎን ይጥላሉ። ዮሐ.6:35-59

ዘላለም ማለት እኮ አሥር፣ ሃያ፣ ወይም ሰማንያ ዓመት ማለት አይደለም፤ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና" የሚለውንም መለኮታዊ የነጻነት አዋጅ ይዘነጋሉ። ሮሜ 8:1-2።

"እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኮንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔርም ቀኝ ያለው ደግሞም ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" በማለት የጸና የአማላጅነት ቃል ኪዳን በክርስቶስ እንዳለን ያረጋግጥልናል። ሮሜ 8:31-39፣ መዝ.89:1-3 በማስተዋል ያንብቡ።

መጽሐፍ ቅዱስ፡- "ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም" ስለሚል ከክርስቶስ ደም በስተቀር ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅ የሚችል ሌላ ሕያው አማላጅ የለም። ዕብ 7:15-28፣ ምዕ 9:14 ቁ.22 ፩ጴጥ 1:18-21፣ ሐዋ.ሥራ 20:28። የመዳን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን የሚዘነጉ ሁሉ በቆላስያስ 2:16 ያለውን የአዲስ ኪዳን መንገድ ይስታሉ። ኤፌ 2:1-22 በማስተዋል ያንብቡት።

ሐዋርያው ዮሐንስ፡- «ከእርሱ ጋር ሕብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም ነገር ግን



እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፣ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፤ ኃጢዓት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢዓታችን ብንናዘዝ ኃጢዓታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» ይላል። ፩ዮሐ. 1:6-10።

"ልጆች ሆይ፣ ኃጢዓትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢዓትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኃጢዓታችን ማስተስሪያ ነው ለኃጢዓታችንም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢዓት እንጂ" በማለት የማይረታ ጠበቃና ዋስ ክርስቶስ እንዳለን በማይዋሽ ቃሉ አረጋግጠልናል። ፩ዮሐ 2:1-2። «እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባና ወንበዴም ነው» በማለት በሌላ አማላጅ ወደ እግዚአብሔር ቤት መምጣት ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑን ያረጋግጣል። ዮሐ 10:1

ብጽዕት ድንግል ማርያም እንኳን በምድር እያለች በቃና ዘገሊላ ለማማለድ ሞክራ ከኢየሱስ የተሰጣት መልስ፡- «አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?» የሚል ስለነበር «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» አለቻቸው ይላል። ዮሐ 2:4-5 ስለዚህ ኢየሱስ ያለንን ብቻ ማድረግ ይገባናል።

ኢየሱስ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሎ ሌላውን በር በራሱ ዘግቶታል። ዮሐ 14:6 ሰው ሁሉ ዋስትና ያለው ጠበቃ እያለለት ለምን በከንቱ ይባክናል?

በዮሐ 10:1-12 ደግሞ፡- በበሩ (በክርስቶስ) ሥጋና ደም በኩል ካልሆነ በቀር በሌላ ፈጽሞ መግባት እንደማይቻልና እርሱን ካልያዙ መዳን እንደሚቀርባቸውም አረጋግጠ አስጠንቅቆአል። በጎቹ ግን በበሩ በክርስቶስ



ሥጋና ደም በኩል የመግባት ዕድል አላቸው። ሰው ሁሉ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ መሆኑን ረስቶአል።

ቃሉ፡- "አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው (አማላጅ) ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ" በማለት ኃጢአተኛውን ከመለኮትነቱ ጋር የሚያስታርቅ የክርስቶስ ሥጋና ደም በመካከላችን እንዳለን አረጋግጠልናልና፤ ሳናወላውል በቃሉ ታምነን ልንድንበት ይገባል።

አንዳንድ ሰዎች መላዕክት ስለሚያማልዱ ልመናና ስግደት ሊቀርብላቸው ይገባል ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ፡- እያንዳንዱ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው፣ ያለምንም ልመና መልአክ በአጠገቡ እንዳለውና ከክፉ ነገር ወይም ከሰይጣን እንደሚታደገው ይናገራል። ማቴ 18:10፣ መዝ 34:7። 19:1-16፣ ዘካ 3:1-10። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ምዕመኑ እግዚአብሔርን የሚወድና የሚፈራ አንድ አምላክንም ብቻ የሚያመልክ ስግደትም ለአንድ አምላክ ብቻ መሆኑን የሚያምን የሆነ እንደሆን ብቻ ነው። ኢሳ. 42:8፣ ዘካ 3:1-8፣ መዝሙር 34:6-10፣ ሐዋ.ሥራ 5:17-21፣ ምዕ 12:6-11 መላእክት ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያውቃሉና፤ መላእክት እንዲሰገድላቸው አይፈቅዱም። ራእይ 19:9-10፣ ምዕ 22:8-9። መላዕክት የንስሐ ልብ የሌለውን ኃጢዓተኛ አይወዱም። እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ሊቀስፉ ሲልካቸውም አይምሩም። ፪ነገ.19:35-37፣ ሐዋ.ሥራ 12:23። መላእክት፡- እኛ እውነተኞች የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስንሆን ከእግዚአብሔር ተልከውልን የሚረዱን ከአደጋም የሚጋርዱን ረዳቶቻችን ናቸው። መዝ 91፣ ዕብ 1:14። ከመለኮት ጋር የማስታረቅ ቃል ግን በወንጌል በኩል በክርስቶስ